# ለሀገርና ለህዝብ ችግር መፍትሄ ለመሻት

## <u>በቅድሚያ</u>

## እራስን ከችግር ፈጣሪነት መግታት!!

ጅብ በማያውቁት አገር ሄዶ ቆዳ አንጥፉልኝ ማለቱ የቆየና የነበረም አባባል ነው። ይህ አባባል ዛሬም በሀገራችን ሁኔታ ይሰራል። ከወያኔ ጋር አስረሽ ምቺው ሲሉ የነበሩና፣ወያኔን ሲያቋቁሙ የከረሙ፣ህዝብን በተለያየ መንገድ ሲከፋፍሉና ሲፈጁ የኖሩትን ጨምሮ፤ዛሬ ደግሞ ዓይናቸውን በምፅዋ ጨው አጥበው፣ መነሻና መሰባሰቢያቸውንም ከኤርትራ አድርገው፣ለኢትዮጵያ ህዝብ ችግር መፍትሄ ሰጪዎች፣እኛ ነን እያሉን ናቸው። የኤርትራ ህዝብ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቱን የተላበሰ ቢሆን ኖሮ፣እኛን ያየህ ተቀጣ የሚል ትምህርትና ምክር በሰጣቸው ነበር። ግን ይህ አልሆነም። አፍጦና አግጦ ያለው እውነት ግን፣ የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ ህዝብ በአምባ ገነኖች መዳፍ ሥር እየማቀቀ ያለ መሆኑ ነው። እነዚህ የኛ ጉዶች ለሁለት አምባገነን ገዢዎች እየታዘዙና እያገለገሉ ያፈሰሱት የነፁሃን ደም ሳይደርቅ፣ያቋቋሙት የወያኔ መንግሥት ሳይወድቅ በትረ መንግሥቱ ለኛ ይገባል እያሉን ናቸው። የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ መብትን የተላበሰ፣በህዝብ እኩልነት ላይ የተመሠረተ አዲስ ቤት ሠርቶ ባንድነት መኖር የማያሻ፣የማያምርበትም ይመስል! የወያኔን የዘር ፌዴራሊዝም፣እኛ በምንለው፤ የሀገራዊ ለዓላዊነት÷<u>ባላና ምሰሶ</u> በተነፈገ ፌዴራሊዝም እንተካላችሁ እያሉን ናቸው። እሣት ካየው ምን ለየው ብሎ መጠየቁ ወቅታዊና ተገቢም ነው።

የሰሞኑ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ቃለምልልስ፣በየፓልቶኩና በአሥመራም ድግሥ፣የባዕዳን ደጋፊዎቻቸውም ትርምስ፤ይህንኑ ዳግማዊ ሤራ አመልካች፣ወያኔን ለማዕከላዊ ሥልጣን፣ኤርትራን ለግንጠላ ያደረሰውንም ሤራ አስታዋሽ ነው። ምፃት

ይሉዋል ይህ ነው። ጆሮ አይሰማው የለ ይባል አይደል!! መቼስ ምን ይደረግ እንሰማቸዋለን።

ዛሬ ወያኔ በሚገዛት ኢትዮጵያ፣የኢትዮጵያ ዜጋ የሚል ቁምነገር አይሰማበትም። ህገመንግሥቱም ይህንን ያካተተ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ ነው፣ ዜግነቴ ኢትዮጵያዊ ነው ብሎ እራሱን የሚገልፀው እንጂ፣የወያኔ ህገ መንግሥት የዜግነትን መብት የሰጠው የያንዳንዱ ጐሣና ክልል ነው። ፍርድ ቤቶች፣ መንግሥታዊ ተቋሞች፣ት/ቤቶች፣ ማህበሮች...ወ.ዘ.ተ. እንዲጠቀሙበት የተደረገው የጐሳ ዜግነት መታወቂያ ብቻ ነው።

ይህ አንድ ሕዝብ የሚኖርባት፣የጋራ ታሪክና ባህል በጋራ ያደገባት፣ክፉና ደግንም በጋራ አይቶ የጐደሉትን ለሟሟላት ተካቶ የሚኖርባት፥<u>ላዓላዊት ኢትዮጵያ አልነበረችም፣ መኖርም የለባትም የሚል ዓላማ ይዞ፣</u> ኢትዮጵያን በሁሉ አቅጣጫ ለመበተን ታልሞ የተነደፈ <u>**የዘረኛ ብሄርተኛ ፖለቲካ**</u> ነው። ይህ በጐሰኝነት ላይ የተመሠረተ የዘረኛ ብሄርተኝነት ፖለቲካ፣ከጥንስሱ ጀምሮ ወያኔና ሻቢያ ኢትዮጵያን ለመበታተን በጋራ የነደፉትና በጋራም የተዋጉለት መሆኑን ዛሬ ማን አሌ ሊል ይችላል? የሰው ልጅ ሁኔታዎች ካልተመቻቹለትና ዕድሉንም ካላገኘ የተወሳሰቡ ሁኔታዎችን መገንዘብ ሊከብደው ይችል ይሆናል። ሻቢያና ወያኔ ተባብረው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የጣሉትን መከራና፣ኢሳያስ አፈወርቂ "የመቶ ዓመት የቤት ሥራ እንሰጣችኋለን" ያለውን አባባል ዛሬ እየተካሄደ ካለው ሁኔታ ጋር አዛምዶ ማየት ግን የሚከብድ መሆን የለበትም። ዛሬም የኤርትራ ገዢ ቡድን ለኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ የተለየ ቅዱስ እቅድና ዓላማ አለው ብሎ መገመትም ሆነ ማሰብ የዋህነት፣ዳግም መሞኘትም ይሆናል። እዚህ ላይ ብዙም መነጋገር አያስፈልግም "ከእባብ እንቁላል እርግብ አይጠበቅም" ብሎ መዝጋቱ ይመረጣል።

የዘርና የጐሣ ፖለቲካ በወያኔም ሆነ በሌሎች ተቃዋሚ ነን በሚሉ ቢነሳ መሠረታዊ መለኪያው ተመሳሳይና ተወራራሽ ነው። የአንድ አገር ህዝብ ቀዳሚና ዋናው መተሳሰሪያና መሰባሰቢያ ከየብሄሩ ጋር የሚኖረው ግንኙነትና ትሥሥር ነው ብለው የሚያምኑ ስለሆኑ፣ሁሉን የሀገሪቷን ዜጐች ባንድነት የሚመለከተውንና የጋራ መፍትሄ የሚሻውን የዴሞክራሲና የሁለገብ መብት ትግል በሁለተኛ ደረጃ ያስቀምጣሉ። ህዝብን በአጠቃላይ ለሚያስተሳስሩ እውነታዎችና እሤቶች ዝቅተኛ ዋጋ የሰጧቸዋል። የብሄሮችና የብሄረሰቦች ችግር በሀገሪቱ በአጠቃላይ የዴሞክራሲያዊ ሥርዐት አለመስፈን ውጤት መሆኑንም የማይቀበሉ ስለሆነ፣ ቀዳሚና ዋነኛው በሆነው አገር አቀፍ ዴሞክራሲያዊ ትግል ሥር ከመሰባሰብ ወደየብሄራቸው መመለስን ይመርጣሉ። ይህ እውነት የሁሉም ብሄርተኛ ድርጅቶች የጋራ ባህሪ ነው። ይህ ስለሁነም ነው ለነሱ አገርን በብሄር ፌደራሊዝም መከፋፈል አንገብጋቢ ጥያቄ ሆኖ የሚቀርበው።

በአንድ አገር ለዘመናት የኖረና በቀጣይነትም ችግሮቹ ተወግደው በጋራ መኖር ይጠቅመዋል የምንለው ህዝብ፣ከየራሱ ብሄር ጋር ብቻ ሳይሆን፣ በሙያ፣ በተፈጥሮ ሀብት፣በታሪክ፣ በልምድና ባህል፣ በጋብቻ...ወ.ዘ.ተ. ከተቀሩት ብሄሮችና ህዝብ ጋር የተሳሰረ ነው። እነዚህ ሁሉ ተደምረው ነው ህዝብን እንደ ህዝብ የሚገልፁት። ለህዝብ ችግር ዴሞክራሲዊ መፍትሄ ሲፈለግም እነዚህን ሁሉ አካቶ ነው። ሁሉም ብሄርተኛ ድርጅቶች ይህንን አወንታዊ ትሥሥር አይቀበሉም። ይህ በመሆኑም ነው በሁሉም ብሄርተኞች የዴሞክራሲና ሁሉን ያካተተ የመብትና የአንድ አገርና የዛን አገር ህዝብ የለዓላዊነት ጥያቄዎች የማይቀበሉት ወይም ቅድሚያና ክብደት የማይሰጧቸው። ከሁሉም በላይ በአንድ አገር ለሚኖርና ለኖረም ህዝብ ዴሞክራሲያዊና ሁለገብ መብት፣ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መምጣት፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ ለዓላዊነት ማስገኘት፣በብሄር መደራጀት ጠያቄ

አለመሆኑን አይቀበሉም። እውነቱ ግን ለህዝብ መብት መታገልና ለፍትዓዊ ሥርዐት መቆም በብሄር ወይም በጐሣ ክልል መጐዳጀትን ጠያቂ አይደለም።

ነገርን ነገር ያነሳዋል ይባላልና፣እነዚህን ብሄርተኛ ድርጅቶች እያሰለጠነና መጠለያ ጭምር እየሰጠ የሚያሰማራቸው የኤርትራው አምባገነን፣ በኤርትራ ከዘጠኝ ያላነሱ ብሄሮችና ብሄረሰቦች እንዳሉ ቢታወቅም "አንድ አገር አንድ ህዝብ፣አንድ ህዝብ አንድ ልብ" የሚል ከመብትና ከዴሞክራሲ የተነጠለ አደናጋሪ ዘፈን አስወጥቶ! ሁሉንም ባንባገነን ክንድ ሥር አዋላቸው እንጂ፣በየብሄራችሁና በየጐሣችሁ ተደራጅታችሁ ዴሞክራሲያዊ መብታችሁን አሰጠብቁ አላላቸውም። ወያኔም በትግራይ ይህንን አላደረገም። ታዲያ! እነሱ ይህ ለኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ነው የሚሰራው ሲሉን፣እኛ ደግሞ ያልጠረጠረ ተመነጠረ፣ዱላ ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ብንል ጥፋታችን ምኑ ላይ ነው??

በዚህ አኳያ ባለፉት አርባ ዓመታት ከየብሄሩ ተወጣጥተው የጐሣና የዘር ክልል ሳያግዳቸው ለተሟላ ሀገራዊና ህዝባዊ መብት ሲታገሉ የወደቁ ሰፊፍ የህዝብ ልጆችና የሀቀኛ መብት ተሟጋቶች ትተውልን ያለፉትን ፈር ቀዳጅ ምሳሌነት ማስታወሱ ወቅታዊና ተገቢም ነው።

በአንድ አገር ለሚኖር ህዝብ ዴሞክራሲያዊና የተቀሩትም የመብት ዓይነቶች መሟላት የሚታገል ድርጅትም ሆነ ዜጋ፡-የኦሮሞ ህዝብ ቁጥር ይህን ያህሉ የተፈጥሮ ሀብትም የዚሁ ብሄር ወይም የዛኛው ብሄር ወደሚል አነጃ ግራንጃም መግባት አያሻውም። ከዚህ ወይም ከዛኛው ብሄር ለመወለድ በግል ያደረግነውም አስተዋፅኦ የለም። ከማንኛውም ብሄር መወለድና አለመወለድ የአጋጣሚ ጉዳይ ብቻ ነው። የመብት ጥያቄ የአሃዝ መብዛት ወይም ማነስ ጉዳይም ተደርጐ መወሰድ አይችልም። ለዚህኛው ብሄር ተሰጥቶ፣ወይም እንዲኖረው ተገርጐ ለሌለኛው ብሄር አባል የሚነፈግ የመብት ዓይነት የለም። ተፈጥሮ በአንድ መልክአ-ምድር ለሚኖር

ህዝብ ያደለው በረከት በዛ መልክአ ምድር ለሚኖር ህዝብ በአጠቃላይ የተሰጠ ፀጋ እንጂ፤ ዘርና ጐሳን በመከፋፈል የተሰጣችው ገፀበረከት ተደርጐም ሊታይ በጭራሽ አይገባም። አይቻልምም።

ዛሬ በሀገራችን በተቀዋሚነት ተሰልፈናል የሚሉን ብሄርተኛ ድርጅቶች እንደሚሉን ቢሆን ኖሮ፡- በደቡብ አፍሪቃ ያለው የተፈጥሮ ሀብት በሞላ (ወርቅ፣ ዲያመንድ፣ኮፐር፣ኮልታን፣ ብረት...ወ.ዘ.ተ.) እንዲሁም የጫካና የባህር ፀጋ በምላ የጥቂሩ ህዝብ ሀብት ብቻ ተደርጐ በተወሰደና የተቀረው ዜጋ ከነዚህ የተፈጥሮ ፀጋዎች ተገሎና ታግዶ እንዲኖር በተገደደ ነበር። በብሄርና በጐሣ ፌዴራሊዝም መበለት የዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት ሊሆን ቢችልማ ኖሮ፣ለዘመናት ቅኝ ግዛት ተደርጐ የኖረና ከ76 ያላነሱ የተለያዩ ብሄረሰቦችና ብሄሮች ያሉበት፣ህንዶች፤ ነጮች፣ድብልቅ የቆዳ ቀለም ያላቸው ባንድ ከተው የሚኖሩባት ደቡብ አፍሪቃ፤ቅኝ ግዛት መደረጓንና ለከፋም ብዝበዛና ምዝበራ የተጋለጠች መሆኗን እንደ ባንዲራ እያውለበለበች፤ጥቁር፣ነጭ፣የዚህ ወይም የዛኛው ጐሳና ብሄር ...ወ.ዘ.ተ. በማለት በተለያዩ የብሄርና ብሄረሰቦች ፌዴርል መንግሥታት ተከፋፍላና ተበልታ ተፈጥሮም፤ያችን ድንቅና ውብ አገር ያደለቻቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች የዚህኛው ወይም የዛኛው ብሄር ንብረት እየተባሉ በተሸነሸኑ ነበር።

የደቡብ አፍቂካ ታጋዮች እንደኛዎቹ ፅንፈኛ ብሄርተኞች፤በዚህ ክልል ያለው የተፈጥሮ ሀብት የዚህ ወይም የዛኛው ብሄር ንብረት ነው አላሉም። በዚህ አጋጣሚ በተራዘመው የደቡብ አፍቂካ ሕዝብ የትግል ዘመን የተነደፈውንና የትግላቸው መርህ በመሆን ያገለገላቸውን የነፃነት ማህደር (Freedom charter) ልጠቅስ እወዳለሁ። ማህደሩ እንዲህ በማለት ይጀምራል፡-

"The national wealth of our country is and will be the heritage of all South Africans, and will be restored to the people. The

mineral wealth beneath the soil, the banks and monopoly industry shall be transferred to the ownership of the people as a whole.

We the people of South Africa, declare for all our country and the world to know: that South Africa belongs to all who live in it, black and white, and no government can claim authority by any other means unless it is based on the will of the people."

ይህ ማህደር፤በዘር በቆዳ ቀለም፤በብሄርና ብሄረሰብ መብትን አስገኛለሁ የሚለውን ፅንፈኛ አመለከከትን እንዳለ የቀበረና በዴሞክራሲዊ ትግል ቀዳሚነት የሀገሪቷን ህዝብ በአጠቃላይ ሁለገብ መብቱን ለማስከበርና የሀገሪቱን ለዓላዊነት በዚህ ላይ ለመመስረት የተገባ ቃል ኪዳንና እንደትግል መሣሪያነትም ያገለገለ ማህደር ነው።

በዚህ ማህደርም ሆነ ዛሬ ባለው የደቡብ አፍሪቃ ህገመንግሥት የኮሳ ብሄርና (ህዝብ) የተቀሩት የደቡብ አፍሪቃ ህዝቦች፣የዙሉ ህዝብና የተቀሩት የደቡብ አፍሪቃ ህዝቦች...ወ.ዘ.ተ. የሚል ብሄርተኝነትን የሚያቀነቅን ስንኝ ወይም ሀረግ ሰፍሮ አይታይም።

ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብት መሟላት እንታገላለን፣ለዘላቂ ሠላም መገኘትና ለህዝቡ የጋራ ብልፅግና ከንጀት እናለቅሳለን የሚሉ ድርጅቶችና ዜጐች፣ከዚህ መሰሉ እውነት የመማርና ከኢትዮጵያ ህዝብ መሠረታዊ ፍላጐቶች ጋር ማጣጣም ይጠበቅባቸዋል። ይገባልም። ከወያኔ የዘርና የጐሣ ፌዴራሊዝም መላቀቅ ወቅቱ አሁን ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጐት አንዱን የጐሣ ፌዴራሊዝም በሌለኛው የጐሣ ፌዴራሊዝም መተካት ሳይሆን፣ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠርቶ ማንኛውንም

ዓይነት ጭቆናና ብዝበዛ በማስወገድ ሁለገብ እኩልነትን አስፍኖ በጋራና በሰላም አብሮ ለመኖር ነው። የ97ቱም ምርጫም ይህንኑ ፍላጐቱን ጠቋሚ ነው።

ሌለኛው በሰሞኑ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ፣እንዲሁም የፓልቶክ ውይይት ወያኔን ተቃዋሚ ነን በሚሉ የብሄር ድርጅቶች እየቀረበ የመወያያ ነጥብ ሆኖ ያለው፣ የግለሰብና የቡድን መብት የሚለው ነው። ግለሰብ የሚለው ግላሰቦች ሊኖራቸው የሚችለውን የመብት ዓይነት ጠቋሚ ሲሆን (ዝርዝር ይዘቱን ያላብራራ ቢሆንም) የቡድን መብት የሚለው ብሄረሰቦችና ብሄሮች ሊኖራቸው የሚችለውን የመብት ዓይነት አመልካች ነው። ጥያቄው በአንድ አገር የሚኖረው ህዝብ መብቱን የሚያገኘው ወይም የሚባደነው ከራሱ ብሄር ብቻ ነው? ወይስ ሊሎች ህዝቡን በጋራ የሚያባድኑና የሚያስተሳስሩት፣ብሎም እንደ አንድ ህዝብ የሚገልፁት ሊሎች ክስተቶች አሉት የሚለው ነው። አሉት የምንል ከሆነ ደግሞ ለምን ሁለቱ የግንኙነት ዓይነቶች ብቻ የመብት መግለጫዎችና መሥፈርቶች ሆነው ተመረጡ ወይም ቀረቡ የሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ ሊያገኙ ይገባል። በአንድ አገር ለዘመናት አብሮ የኖረ ህዝብ፤የታሪክ፣የባህል፣የጋብቻና፣የሥነልቦና ትሥሥር፣በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ይዘትና ቅርበት ወ.ዘ.ተ. ላይ ሁሉ ተመስርቶ ቅርርብ ይፈጥራል፣ይባደናል መብቱንም ያስከብራል። ለምሳሌ ያህል አንድ የአማራ ብሄር አባል ከበርቴና ባለኢንድስትሪ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ለማስጠበቅ ከድሃ የአማራ ብሄር አባላት ጋር ከመባደንና ከማበር አቻዎቹ ከሆኑት የኦሮሞውና የትግሬው ባለሀብትና ባለኢንዱስትሪ መተባበርና መተሳሰር የበለጠ መደባዊ ጥቅሙን ያስጠብቅለታል። የኦሮሞ፣የትግሬውና የአማራው ድሃ ገበሬዎች ከየራሳቸው ብሄር ከመጡ ከበርቴዎች ጋር ከመደራጀት እርስበርሳቸው ቢተሳሰሩና በጋራ ቢደራጁ የበለጠ መደባዊ ጥቅማቸውን ያስጠብቃሉ ወ.ዘ.ተ. ይህን መሰሉ ብሄር ዘለል የህዝብ ትሥሥር፣ ታሪካዊ እውነታና ዘመናት ያከተተ ማህበራዊና የተዋልደ ግንኙነቶች ወ.ዘ.ተ.

ህዝብን እንደ ህዝብ ገላጭ መሥፈርቶች ሆነው እንደሚያገለግሉ፣ወድፊትም ለምንፈልገው ዴሞክራዲያዊ ሥርዐት ግንባታ መሠረት መሆናቸውን ማናቸውም ብሄርተኛ ድርጅቶች አይቀበሉም። ያለፈው ሁሉ ጨለማ ነው፣ያለፈው ሁሉ ጭቆና ነበር የሚል ድምዳሜ ስለደረሱ፣ህዝብን በሺዎች መንገድ ላስተሳሰሩና ለሚያስተሳስሩ መሥፈርቶች ባይተዋር ለመሆን በቅተዋል። ይህንን መሠረታዊ ሁኔታ በአግባብ ባለመገንዘብም ይመስለኛል የኢትዮጵያን ቀዳምት ጀግኖች ኮሎኒያሊስቶችን አሳፍረው የመለሱ የአፍሪካን ብርቅዬ ልጆች እነጐበናን፣ሀብተ ጊዮርጊስን፣ባልቻ አባነብሶን፣ገበየሁ ገባን እንዲሁም እነ ጀኔራል ጃጋማኬሎን፣ እንዲሁም ሌሎችን ጀግኖች ያልሆነ ስም የሚሰጧቸውና ካለቦታቸው የሚያስቀምጧቸው። ይህ ብሄርተኛ ባህሪያቸውም ነው ያለፈው ዘመን ከዛሬው ዘመንና ትውልድ ጋር ያለውን ግንኙነትና ትሥሥርም ለማየት እንዳይችሉና፣የቡድን መብትም ለነሱ የአንድ ብሄር አባል መሆን ወይም አለመሆን ጋር ብቻ ተያይዞ የሚታየው።

የዲሞክራሲ ጥያቄና ትግል ከብሄር ጥያቄና ትግል የሰፋና የላቀም ነው ሲባልም፤የዲሞክራሲ ትግል የአንድ አገርን ህዝብ ሁለገብ ትሥሥር ዋጋ ሰጥቶ፣ ለህዝብ የጋራ ታሪክ ቦታ አስገኝቶ፣ልምዱንና ባህሉን፣በጋብቻና በሌሎች መንገዶችም በዘመናት ውስጥ የተፈጠሩና ያደጉትን የግንኙነት ዓይነቶች አጠቃሎ ለማየት ብቃት ስላለው ጭምር ነው። የዛሬው ዘመን ትውልድ የያዘው አስተሳሰብና ስነልቦናዊ አመለካከቱ ጭምር ካለፈው ትውልድ አስተሳሰብና ባህላዊ አመለካከት ጋር ግንኙነት ያለው ስለሆነ፣አጠቃላይ ዕይንታ ያለው ሀገራዊ የዴምክራሲ ትግል ሁለቱን ትውልድ አያይዞ ለማየት የሚያስችል ሁነኛ ድልድይም ነው።

ይህ እውነት ስለሆነም ነው፤የብሄርና የብሄረሰቦች ጥያቄ የዴሞክራሲ ጥያቄ አካል ሆኖ የሚቀርበው። ተቃራኒው ግን ሥህተት ነው። በሀገራችን ብሄርተኛው

የወያኔ ቡድን ለማዕከላዊ ሥልጣን መድረስ በትግራይ ለሚኖረው ብሄርና ብሄረሰቦች ያስገኘው መብት፣ያላበሳቸው ዴሞክራሲ የለም። የንጉሡ ፊዩዳላዊ አገዛዋም ለፖለቲካ መነገኛ ካልሆነ በቀር ገደል ውስጥ ለሚኖረው ድሃ የመንዝ አማራ ያስገኘው ብልፅግና የሰጠውም መብት አልነበረም። ጭቆናና ምዝበራን ግን በሀገር ደረጃ አስፍኗል። ወያኔም ይህንኑ እያደረገ፤እንደ ሀገረና እንደ ህዝብም የመኖር መብታችንን ጭምር እየተፈታተነን ነው። ነገም ሆነ ተነጐዲያ ሌላው ብሄርተኛ ቡድን ለመአከላዊ ስልጣን ቢደርስ መንገዱ ተመሳሳይና ተወራራሽ ነው። የዓለም ህዝቦች ተመክሮም በዚህ አኳያ ሌላ የተወልን ትምህርት የለም።

ሰሚና እውነተኛ ፈራጅ አጣ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብም ከሰሜን እስከ ደቡብ (ኤርትራንም ጨምሮ) ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ይህንኑ እውነት በግልፅም ሆነ በስውር እያስተጋባ ነው። አገሬን፣ታሪኬን፣ሁለገብ ዴምክራሲያዊ መብቴን ለራሴ በራሴ ነው ማዕከላዊ መልዕክቱ። ዘመኑ ዘመነ ተጋላቢጦሽ ሆነና ከተማሪው አስተማሪው በዝቶ የተወናበደው ተበራከተ እንጂ፡-በዛሬው ሁኔታ ቀና ልቦናን ይዞ የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጐት ማዳመጡ በበቃ ነበር። ታዲያ! ድህነትን ተላብሶ ካስተማረቸው የኢትዮጵያ ድሃ ህዝብ የበለጠ የሚታዘዙትና የሚያገለግሉት የባዕድ ኃይል ስላለ፣ ከሌሎቹ ምርኮዞቹ ጋር አጣምሮ ተጓዙ ባላቸው መንገድ ለመጐዝ ተገደዋል። ወያኔን ለስልጣን ያደረሰው የ1991ዓ.ም. የለንደኑ ስብሰባም ተመሳሳይ ሂደት የተከተለና በአብዛኛውም ተመሳሳይ አጃቢዎች የነበሩትም ነው።

ወያኔን የመሰለ ዘረኛ ቡድንን፡-በዘርና በጐሣ አልደራጅልህም ብሎ ገትሮ የያዘው ያ የናቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። የዘርና የጐሳ ድርጅቶች ማዋቀርና መፍጠር ስላልተቻለና ስለተሳነውም ነው ኮቲ እያባዛ፤ ወደ መብት ማስከበር ሳይሆን ወደ ጅምላ ግድያና ፍጅት የተሸጋገረው።

ሌሎችም የጐሣና ብሄርተኛ ድርጅቶች ሊያድጉና ሊመነደጉ ያልቻሉት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጐትና መልዕክት ቁልጭ ብሎ እየታየ ያለና የተቀመጠም ስለሆነ ነው። ዋነኛው ቁምነገር ግን ዛሬም ሆነ ወደፊት የህዝብ ምልዕክት ትክክለኛ አነባቢ፣ቀራጥና ህዝባዊ ተርጓሚም ያሻዋል። ይህ ሊሆን ካልቻለ ዴሞክራሲያዊ ትግሉ ይጫጫል። የህዝባችን የሥቃይ ዘመንም ይራዘማል። ለዚህም ነው!! ለሀገርና ለህዝብ ችግር መፍትሄ ለመሻት በቅድሚያ እራስን ከችግር ፈጣሪነት መግታት የሚለው የአያት ቅድመአያቶቻችን ምክር ወቅታዊ ሆኖ የሚገኘው።